# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ረቂቅ
## ማብራሪያ

ሕዳር 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ የማሻሻያ ረቂቅ ማብራሪያ

1. **መግቢያ**

የ2010 ዓ/ም አገራዊ ለውጥን ተከትሎ መከላከያም የሪፎርም ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደትግበራ በመግባት በርካታ የሪፎርም ስራዎችን ማከናወኑ ይታወቃል። መከላከያ ሠራዊቱ ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት ፍፁም ነፃ ሆኖ የተጣለበትን አገርን የመጠበቅ ተልዕኮ በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲወጣ ለማድረግ ህብረ-ብሔራዊ ተዋፅኦውን የጠበቀ ፕሮፌሽናል ሠራዊት ለመገንባት ማነቆ የሆኑ የህግ ማዕቀፎችና ተቋማዊ አሰተሳሰቦችን በመፈተሽ ማስተካከል አንዱ የሪፎርሙ ስራ አካል እንደነበርም ይታወሳል።

በዚህም በስራ ላይ የነበረውን የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ጨምሮ ሠራዊቱ በየደረጃው የሚመራባቸው ደንብና መመሪያዎችን ተሻሽለው ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል። የሪፎርም ስራ ቀጣይነት ያለው ተግባር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በርካታ ጉዳዮችን አሁን ካለው ሁለንተናዊ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ማየትና መመዘን እንዲሁም መከላከያን በቀጣይነት ሪፎርም የማድረግ ሂደትን አጠናክሮ ማስቀጠል አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንፃር የመከላከያ ሠራዊቱ አዋጅ ማሻሻያዎች ቢደረጉለትም አሁንም በአዋጅ ምላሽ የሚፈልጉ በርካታ ጉዳዮች በመኖራቸው አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፣ ለዚህም ይህ የአዋጅ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

በአዋጅ ማሻሻያው ትኩረት ተሰጥቷቸው ከተካተቱ ጉዳዮች ውስጥ ከጡረታ መውጫ እድሜ አወሳሰንና የጡረታ እድሜ ከማራዘም ጋር በተገናኘ ያሉ ጉዳዮች፣ ከሠራዊት መብትና ጥቅማጥቅሞች አንፃር መታየት ያለባቸው ጉዳዮች፣ የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ጦርነት ሲገጥም የሰራዊት አባል የነበሩትን መልሶ ከመቅጠር ጋር በተገናኘ ስለሚኖረው አፈፃፀም፣ ስለብሔራዊ አገልግሎት፣ በአዋጁ መካተት ያለባቸው ተጨማሪ የሚዳይ አይነቶች እና ሌሎች የአፈፃፀም ክፍተት ያለባቸው ጉዳዮችን ይገኙበታል።

ረቂቁ በስራ ላይ የነበሩትን የመከላከያ ሠራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 እና ቀጥሎ በማሻሻያነት የፀደቀውን ማሻሻያ አዋጅ 1232/2013 መነሻ ያደረገ ሲሆን አዋጁ ባልተበጣጠሰ መልኩ ለሠራዊቱ በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆንና ለአረዳድም እንዲመች ለማድረግ ማሻሻያው በአንድ ባጠቃለለ መልኩ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። ይህ የህግ ማብራሪያ የተዘጋጀውና መነሻ ያደረገው በአንድ ተጠቃሎ የተዘጋጀውን የአዋጅ ረቂቅ ሲሆን በዋናነት ማሻሻያ በተደረገባቸው ጉዳዮች ላይ ግልፅ ለማድረግ ማብራሪያው እንደሚከተለው ቀርቧል።

2. **በረቂቅ አዋጁ የተደረጉ ማሻሻያዎች**

**2.1.** ***<u>አንቀፅ 2፡- ትርጓሜ፡-</u>*** በትርጉም ውስጥ የተካተቱ ቃላት ወይም ሀረጋት በንዑስ አንቀፅ 11 የተጠቀሰው "በክብር የተሰናበተ" እና "ፊልድ ማርሻል" ከሚሉት በስተቀር ሁሉም የነበሩ ናቸው። ሆኖም ግን  እንደ መስመራዊ መኮንን፣ ከፍተኛ መኮንንና ጀነራል መኮንን የተሰጠው ትርጉም ምድር ኃይልን ብቻ ማዕከል ያደረገ ስለነበር በአየር ኃይልና በባህር ኃይል ያሉ አቻ የማዕረግ ደረጃዎችን ታሳቢ በሚያደርግ መልኩ በማሻሻያው ትርጓሜው እንዲስተካከል ተደርጓል።

በሠረዊቱ ማሻሻያ አዋጅ 1232/2013 ከሙሉ ጀነራል ማዕረግ በላይ አዲስና ከፍተኛው የማዕረግ ደረጃ እርከን እንደሚኖር መደንገጉን ተከትሎ በጥናት መሰረት ከሙሉ ጀነራል ቀጥሎ ፊልድ ማርሻል የማዕረግ ደረጃ እንዲኖር መወሰኑ ይታወቃል። በመሆኑም የፊልድ ማርሻል ማዕረግ ትርጓሜ በትርጓሜ ውስጥ በንዑስ አንቀፅ 8 ላይ እንዲካተት ተደርጓል።

በንዑስ አንቀፅ 11 "በክብር የተሰናበተ" የሚለው ሀረግ እንዲሁ በተመሳሳይ እንደአዲስ የገባ ሲሆን በአዋጁ ይዘት ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ድንጋጌ በመሆኑና ለፈፃሚው አካል አሻሚነት እንዳይኖረው በትርጉም ግልፅ ተደርጓል።

**2.2.** ***<u>አንቀፅ 4፡- ስለመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀት</u>***፡- በህገ መንግስቱ አንቀፅ 87 ንዑስ አንቀፅ 3 እና 4 የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መነሻ በማድረግ መከላከያ ሠራዊት በመሰረታዊነት ሊኖሩት የሚገቡ መሰረታዊ ተልዕኮዎችን በተቋሙ የተለያዩ ሰነዶች ላይ ተገልፀዋል። ይሁን እንጂ ይህን ተልዕኮ ለተቋሙ የተለያዩ ሰነዶች

*መነሻ በሚሆነው በሠራዊቱ አዋጅ ማስቀመጡ ተገቢ በመሆኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ* 4 *ስር የመከላከያ ሠራዊት ተልዕኮዎች እንዲካተቱ ተደርጓል።*

**2.3.** ***<u>አንቀፅ</u>*** <u>5 -</u> ***<u>ስለመመልመል፦</u>*** *በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ* 4 *እስከ* 5 *የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደአዲስ በረቂቁ የገቡ ሲሆን በቀጣይ መከላከያ እንደሚኖረው የሰው ሃይል ፍላጎት ከተለያዩ ምንጮች የሰው ኃይል እንዲያገኝ ታሳቢ የተደረገ ነው። ለዚህም መከላከያ በሚፈልጋቸው ሙያ ዘርፎች ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሠለጠኑ ዜጎች በብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ተቀጥረው በሙያቸው ተቋሙን የሚጠቀሙበት ሁኔታ ለማመቻቸትና የብሔራዊ ተጠባባቂ ኃይሉን ለማጠናከርም ፋይዳ በሚኖረው መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎች በረቂቁ ተካተዋል።*

**2.4.** ***<u>አንቀፅ</u>*** <u>7-</u> ***<u>ወታደራዊ ስልጠና፦</u>*** *በአዋጁ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ* 4 *ላይ በማንኛውም ደረጃ ወታደራዊ የሥራ ኃላፊነት በሚሰጥበት ወቅት አባላቱን ለቦታው ብቁ ለማድረግ ስልጠና እና ትምህርት እንደሚሰጥ የሚደነግገው ድንጋጌ አንደኛ ‹‹በማንኛውም ደረጃ›› የሚለው በሁሉም የኃላፊነትና የማዕረግ ዕድገት ስልጠና መስጠት የማያስገድዱ ሁኔታዎች ቢኖሩ እያየ ለመወሰን እንዲቻል ‹‹በማንኛውም ደረጃ›› የሚለው እንዲወጣ ተደርጓል። በዚሁ ድንጋጌ ማስተካከያ የተደረገው ኃላፊነት በሚሰጥበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን የማዕረግ እድገት በሚያገኝበት ወቅትም ትምህርትና ስልጠና እንደሚሰጠው ተካቶ ተቀምጧል።*

**2.5.** ***<u>አንቀፅ</u>*** <u>8-</u> ***<u>ወታደራዊ ቃለ መሐላ፦</u>*** *በዚህ አንቀፅ ከቃለ መኃላ አፈፃፀም ጋር በተገናኘ ያለው ድንጋጌ ማዕከል የሚያደርገው ወታደራዊ ስልጠና ያጠናቀቀ ሆኖ መሰረታዊ ወታደር የሚሆን የሰራዊት አባልን ብቻ የተመለከተ ነበር። ነገር ግን ዕጩ መኮንን ስልጠና አጠናቆ መኮንን ሲሆን ቃለ መኃላ ስለሚፈፅም የህግ ማዕቀፍ እንዲኖረው በማሻሻያው እንዲካተት ተደርጓል።*

**2.6.** ***<u>አንቀፅ</u>*** <u>10 -</u> ***<u>የአገልግሎት ዘመን እና እድሜን በተመለከተ፦</u>*** *ማንኛውም የሠራዊት አባል ውትድርና አገልግሎት ለመስጠት ሲቀጠር የበታች ሹም ከሆነ ለ*7 *አመት፤ መኮንን ከሆነ ደግሞ ለ*10 *አመት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ እንዳለበት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ* 1 *እና* 2 *ተገልጧል። በመሰረታዊ ወታደርነት የተቀጠረ አባል* 7 *ዓመት የማገልገል ግዴታው እደተጠበቀ ሆኖ አባሉ የልዩ ሙያ ባለቤት ከሆነ ግን የሙያተኛ ፍሰቱን ለመቀነስና መከላከያም ለአባሉ ያወጣውን ወጪ መጠቀም ስላለበት እንደመኮንኑ አስር ዓመት አገልግሎት ግዴታ እንዲኖረው ተደርጓል።*

*በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ* 4 *ላይ እንደ አዲስ የተካተተው የ*7/10 *አመት የአገልግሎት ውል ያጠናቀቀ የሠራዊት አባል ከሰራዊት መሰናበት ቢፈልግ የመውጣት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደሚኖሩት ስጋትና የዝግጁነት ደረጃ የ*7/10 *አመት ጥያቄን የሚያዘገይበት ስርዓት መፍጠር ይኖርበታል። ምክንያቱም ምላሽ አሰጣጡ የሚኖረውን የስጋት ሁኔታ ያላገናዘበ ከሆነ የሠራዊቱን የዝግጁነት ደረጃ አደጋ ላይ ይጥላል። በመሆኑም በአደጋ ጊዜ ሚኒስቴሩ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው አባላትን ለመጠቀም የማይችልበት አግባብ ስለሚያስከትል ይህን ክፍተት ለመዝጋት የ*7/10 *አመት ስንብት ጥያቄ እስከ ሶስት አመት ሊያዘገየው እንደሚችል በማሻሻያው ማካተት አስፈልጓል።*

*ሌላው ማሻሻያ ከተደረገባቸው ድንጋጌዎች መካከል በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ* 4 ፣ 5 *እና* 6 *የጡረታ እድሜ ጣሪያ አስመልክቶ ያሉት ድንጋጌዎች ሲሆኑ ዋራንት ኦፊሰሮች* 48 *የነበረው ከከፍተኛ መኮንን* (*ከሻለቃ እስከ ኮ/ል*) *ጋር እኩል ሆኖ ወደ* 52 *አመት ከፍ እንዲል ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት ዋራንት ኦፊሰሮች በውትድርና ቆይታቸው ከፍተኛ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው ሲሆን በቆይታቸው ያካበቱትን ልምድና ተሞክሮ መስጠት በሚችሉበት ወቅት በጡረታ እየተገለሉ በመሆናቸው የጡረታ መውጫ እድሜ ከ*48 *ወደ* 52 *ከፍ እንዲል ተደርጓል።*

*የጀነራል መኮንኖች የጡረታ መውጫ እድሜ በጥቅሉ* 60 *አመት የነበረው እንደማዕረግ ደረጃቸው የተለያየ ሆኖ ብርጋዴር ጀነራል* 56፣ *ሜጀር ጀነራል* 57፣ *ሌተናል ጀነራል* 58 *እና የሙሉ ጀነራልና የፊልድ ማርሻል የጡረታ እድሜ ጣሪያ* 60 *አመት ሆኖ በማሻሻያው ተካቷል። ይህ የሆነበት ምክንያት ጀነራል መኮንኖች የሚኖራቸው የኃላፊነት ደረጃ መነሻ የሚያደርገው በአመዛኙ የማዕረግ ደረጃቸውን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ*

እንደሚኖራቸው የኃላፊነትና የማዕረግ ደረጃ የጡረታ መውጫ እድሜውም ከታች ወደላይ እየጨመረ መሄድ አለበት ከሚል መነሻ ነው። ይህን መነሻ ማድረጉ ባካበቱት ልምድና አቅም መሰረት ተቋሙ አቅማቸውን የሚጠቀምበት ሁኔታ እንዲኖር ከማስቻሉ በላይ የአመራር መተካካት ስርዓቱን ለማሳለጥም ፋይዳ ይኖረዋል በሚል ነው።

የጡረታ እድሜ ማራዘም አስመልክቶ በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1232/2013 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2 የመጋቢ ሀምሳ አለቃና ከዛ በላይ እንዲሁም ለመስመራዊ መኮንን እና ከፍተኛ መኮንን እስከ አምስት አመት ሊራዘም እንደሚችል የሚደነግገውን ከፊልድ ማርሻል ውጪ ያለው በየሁለት አመት ለሁለት ጊዜ ያልበለጠ ሊራዘም እንደሚችል በማሻሻያው ማስተካከያ ተደርጓል። ለምሳሌ አዋጅ 1232/2013 የጀነራል መኮንኖችን ጡረታ እድሜ ስለሚራዘምበት ሁኔታ ሲያስቀምጥ በየሶስት አመት ይራዘማል ሲል ገደብ የሌለው እና ግልፅ አልነበረም። ነገር ግን አሁን በማሻሻያው በየሁለት አመቱ ለሁለት ጊዜ ሲል በየሁለት አመቱ ውሳኔ ሰጪው አካል ሁኔታውን እያየ እንዲወስን አስተዋፅኦ ይኖረዋል ከሚል ማስተካከያ ተደርጓል።

የጡረታ መውጫ እድሜ የማራዘም ስልጣን በአዋጅ 1100/2011 አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 8 መስመራዊ መኮንን ጨምሮ ከመጋቢ አምሳ አለቃ በላይ ያሉት የመከላከያ የሠው ሃብት፣ ከሻለቃ እስከ ኮሎኔል ማዕረግተኛ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም፤ የጀነራል መኮንኖች ደግሞ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ እንደሆነ ይደነግጋል። በማሻሻያው ጡረታ ማራዘም ውሳኔ በአዋጁ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በአግባቡ ተፈፃሚ ለማድረግና የአፈፃፀም ክፍተት እንዳይኖረው የተማከለ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት መከተል ያስፈልጋል በሚል የኢታማዦር ሹሞችንና ኃይል አዛዦችን የጡረታ እድሜ ማራዘም ስልጣን በጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ ከዚህ ውጭ የሆኑት በጦር ሃይሎች ጠቅላይ ኢታ/ሹም ውሳኔ ሰጭነት ብቻ እንዲፈፀም በማሻሻያው ተካቷል።

**2.7.** ***<u>አንቀፅ 12 ለሠራዊት አባላት ስለሚደረግ ማበረታቻ</u>-*** በማሻሻያ አዋጅ 1232/2013 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 4 ከሰባት አመት በላይ ውትድርና ግልጋሎት ያለው ሆኖ በቀላሉ የማይተካ ልዩ ክህሎት ያለው እንዲሁም ሀያ አመትና ከዛ በላይ ያገለገለ ኮሎኔል፣ ጀነራል መኮንንና ከዛ በላይ ያለው ከቀረጥ ነፃ የቤት መኪና መስገባት እንደሚችሉ ይደነግጋል። ማንኛውም የሠራዊት ማበረታቻ እሳቤ ብዙ ላገለገለ በዛው መጠን የአገልግሎቱን ያህል ድጋፍ በመስጠት የሠራዊቱን አባላት ማቆየት፣ ለአገልግሎታቸውም እውቅና መስጠትና ወደሰላማዊ ህይወት ሲመለሱ እንዳይቸገሩ መርዳት ነው። በዚህ መሰረት ከዚህ በፊት የነበረው አሰራር የሠራዊት አባላት ረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ ከማበረታታት አንፃር ውሱንነት ስላለበትና ማበረታቻውም አገራዊ አቅምን ያገናዘበ ባለመሆኑ ማበረታቻውን ወደ 30 አመት ከፍ እንዲል ተደርጓል። በመሆኑም 30 አመትና ከዛ በላይ ያገለገለ ማንኛውም የሠራዊት አባል የቤት መኪና መግዛት ቢፈልግ ከቀረጥ ነፃ መብቱ እንዲጠበቅለት በሚል ተሻሽሏል። ይህን ማድረጉ ከላይ እንደተጠቀሰው ሠራዊቱ ለአገር እየከፈለው ካለው መስዋእትነት አንጻር የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን ማበረታታት፣ እውቅና መስጠትና፤ ሌላው የሰራዊት አባል በተቋሙ ውስጥ ለማገልገል የሚኖረውን ፍላጎት እንዲጨምር ያደርጋል።

ከማበረታቻ ጋር አብሮ የታየው ሠራዊቱ ለአገሩ ውድ የሆነውን ህይወቱን ጭምር እየከፈለ አብዛኛው ዕድሜውን አገሩን በውትድርና እያገለገለ ከቆየ በኃላ በህጉ መሰረት በክብር ከሠራዊት ሲሰናበት ራሱም ሆነ ቤተሰቡ ለማህበራዊ ቀውስ የሚጋለጡበትን ሁኔታን ለማስቀረት 30 አመት እና ከዛ በላይ የውትድርና አገልግሎት የሰጠ የሠራዊት አባል በተወለደበት ክልል ወይም ዞን ከተማ የቤት መስሪያ ቦታ እንደሚሰጠው፤ ሠራዊቱ በማህበር በማደራጀት መኖሪያ ቤት ቦታው ላይ እንዲገነቡ የሚያደርግ አሰራር በመከተል ለማስገንቢያ የተወሰነውን ድርሻ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በገንዘብ እንደሚደጉም በማሻሻያው ተካቷል። ሰላሳ አመት ውትድርና አገልግሎት የሰጠ የሠራዊት አባልን መነሻ የተደረገው ቢያንስ በዚህን ወቅት ጡረታ መውጫ ጊዜ መቃረቢያ ስለሚሆን በጡረታ ሲሰናበት በመኖሪያ ቤት እጦት የትም እንዳይወድቅና እንዳይቸገር ለመደገፍ ታሳቢ ተደርጎ የገባ ነው።

**2.8.** ***አንቀፅ 14- <u>በሀገራዊ ዳግም ጥሪ ስለማገልገል</u>-*** ሠራዊቱ የመደበኛ ውትድርና አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ በተለያየ ምክንያቶች በክብር ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደሚሰናበት ይታወቃል። ነገር ግን አሁን እንደገጠመን አይነት ችግር የሀገርን ሉዓላዊነትን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ

ወይም መንግስት ዳግም ጥሪ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆንበት በስንብት የወጡት አባላት መልሶ የሚቀጥርበት የህግ ድጋፍ እንዲኖር ለማድረግ በማሻሻያ ረቂቁ እንዲካተት ተደርጓል።

**2.9.** **<u>አንቀፅ 15-ስለአግልግሎት ካሳና ጡረታ</u>፡-** በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 እና 6 በማሻሻያው እንደአዲስ የተካተቱት ድንጋጌዎች ሲሆኑ የመጀመሪያው በግዳጅ ላይ የተሰዋ የሠራዊት አባል የጡረታ መብቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ህጋዊ ወራሾቹ ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝ እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት በተለይ በጦርነት ወቅት አባሉ ተሰውቶ ጡረታ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ባለው የጊዜ ክፍተት ቤተሰቡ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች የማያገኙበት (ክፍያው ስለሚቋረጥ) ሁኔታ ስለሚኖር በዚህ ክፍተት ውስጥ ቤተሰቡ ለኢኮኖሚያዊ ችግር የሚጋለጡበት ሁኔታ እንዳይኖር ለማድረግ ታስቦ የገባ ነው። ሌላው በንኡስ አንቀፅ 6 የተካተተው በደረሰበት ጉዳት ባለሙሉ ተጧሪ ጉዳተኛ የሠራዊት አባላት በመንግስት በሚቋቋም የጀግኖች አምባ በዘላቂነት የሚጦሩበትን አግባብ ለመፍጠር ነው። ጉዳዩ በመንግስት ደረጃ የሚፈፀምና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ በመሆኑ በአዋጅ ደረጃ የህግ እውቅና እንዲኖረው ማድረጉ በተደራጀ መልኩ የጀግኖች አምባ ለማቋቋምና ችግሩን በሚፈታ አግባብ ተጎጂዎች የሚጦሩበት ሁኔታ ለመፍጠር ያግዛል የሚል የገባ ነው።

2.10. **<u>አንቀፅ 19 እና 20- ስለ ማዕረግ እድገት እና ደረጃዎች</u> ፡-** በአዋጅ 1100/2011 አንቀጽ 18 የማዕረግ ደረጃዎች አስመልክቶ በመከላከያ ሠራዊት ያሉ ወታደራዊ የማዕረግ ደረጃዎችን ማለትም ከመሰረታዊ ወታደር እስከ ሙሉ ጀነራል ከታች ወደላይ በደረጃቸው ዘርዝሮ ያስቀመጠበት ነበር። ነገር ግን በማሻሻያው የማዕረግ ደረጃዎች በአዋጅ ማስቀመጡ ዝርዝር ስለሚሆን ከዚህ አንጻር በአዋጁ አንቀፅ 18 የነበረው አንቀፅ 19 ሆኖ ዝርዝር የማዕረግ ደረጃዎች በቀጣይ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ የመከላከያ ሠራዊት መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተሟላ ሁኔታ እንዲቀመጥ ለማድረግ በማሻሻያ አዋጅ ረቂቅ አንቀፅ 19 ላይ ዝርዝር ደንብ እንደሚወጣ ጠቅሶ ቢያልፍ በሚል የነበረው ዝርዝር የማዕረግ ደረጃዎች እንዲወጡ ተደርገዋል።

በአዋጁ አንቀፅ 19 ‹‹**የማዕረግ ዕድገት አሰጣጥ**›› በሚለው ርዕስ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ማዕረግ እድገት የመስጠት ስልጣን አስመልክቶ የነበረው ድንጋጌ ከላይ የማዕረግ ደረጃዎች ከአዋጅ ወጥተው በደንብ ይቀመጥ የሚለውን ውሳኔ ተከትሎ የትኛው የማዕረግ ዕድገት በማን ይሰጣል የሚለውም በተመሳሳይ አብሮ የሚታይ በመሆኑ ወደ ደንብ እንዲሄድ ተደርጓል። ነገር ግን በዚሁ ንዑስ አንቀፅ በሚኖረው ወታደራዊ ኃላፊነት የማዕረግ ዕድገት የማፅደቅ ስልጣን የሚኖራቸው የአመራር አካላት ብቻ ገድቦ በመወሰን ቢቀመጥ የትኛው ማዕረግ በማን ይፅደቅ የሚለው የዚህን አዋጅ መፅደቅ ተከትሎ በቀጣይ ተዘጋጅቶ በሚፀድቀው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ላይ የሚዘረዘርበት አግባብ ቢኖር ከሚል መነሻ ነው።

2.11. **<u>አንቀፅ 34- ስለእስር ቅጣት</u>፡-** ወንጀል ፈፅመው ከሁለት አመት በታች እስር የተወሰነባቸው የሰራዊት አባላት በወታደራዊ ማረሚያ ቤት እየታረሙ ቆይተው ፍርዳቸውን ሲጨርሱ ወደሰራዊቱ የሚመለሱበት ሁኔታ ስለሚኖር እነዚህ አባላት በግልፅ በወታደራዊ ማረሚያ ቤት መቆየት እንዳለባቸው፤ ነገር ግን ከሁለት አመት በላይ የእስር ቅጣት የሚያስቀጣ ፍርድ የተወሰነባቸው ደግሞ በመደበኛ ፍርድ ቤት እንደሚታረሙና ቅጣታቸውን ሲጨርሱ ወደህብረተሰቡ የሚቀላቀሉበት ሁኔታ እንዲመቻች ለማድረግ እንዲቻል ሁለቱ አሰራሮች በግልፅ እንዲቀመጡ ተደርጓል።

2.12. **<u>አንቀፅ 35 የወታደራዊ አቃቤ ህግ ስልጣንና ተግባር</u> (በአዋጁ አንቀፅ 34 የነበረ)፡-** በአዋጁ ለወታደራዊ አቃቤ ህግ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባር በተጨማሪ በማሻሻያው የተካተቱት በተቋማዊ ህግ ማዕቀፎች ላይ ጥናት እንዲያደርግ፣ በፍትሃብሔር ጉዳዮች በተቋሙ መብትና ጥቅም ጉዳዮች ወኪል በመሆን አቃቤ ስራ እንዲሰራ፣ በአጠቃላይ በህግ ጉዳዮች መከላከያ ሚኒስቴርን በማማከር እና በመሳሰሉት ስራዎች እንዲሰራ ተጨማሪ ስልጣንና ተግባራት እንዲኖረው በማስፈለጉ ከንዑስ አንቀፅ 4 እስከ 7 ያሉት ድንጋጌዎች በማሻሻያው ተካተዋል።

2.13. **አንቀፅ 37 የቀዳማዊ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን፡-** በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ፊደል ለ/ የእጅ እልፊት፣ ግድያና አካል ማጉደል ወንጀሎች ከመጥቀስ ባለፈ የተጠቀሱት ወንጀሎች በወንጀል መቅጫ ህጉ ያሉበት አንቀፅ ቁጥር ያልተጠቀሰ ነበር።አንቀፅ ቁጥሩን ማመላከት ያስፈለገበት ምክንያት ይህን ለሚያስፈፅመው አካል ይበልጥ ግልፅ እንዲሆንና በእነዚህ በተመላከቱት ወንጀሎች መሰረት የፍርድ ብያኔ እንዲሰጥ ለማስቻል

ይረዳል ከሚል መነሻ ነው። ሌላው በአዋጁ ያልተጠቀሰ ሆኖ በዚሁ ንዑስ አንቀፅ እንደአዲስ የገባው የአለም አቀፍ ህጎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች (በወንጀል ህግ ከአንቀፅ 269-283) በቀዳማዊ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚዳኝበት ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግ ነው። ይህ ፋይዳው የሰራዊት አባላት በተለያየ ቦታና ሁኔታ ግዳጅ በሚስማራበት ወቅት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ እነዚህን አለማቀፍ ወንጀሎች የመፈፀም እድል ስለሚኖረውና ልክ እንደወታደራዊ ወንጀሎች በወታደራዊ ፍርድ ቤት እንዲታይ ማድረጉ ሁኔታው በትኩረትና በአፅንዖት ለመከታተል እንዲያመችና የህጉ መከበር ለወታደራዊ ግንባታ አጋዥ ስለሚያደርገው ከሚል እሳቤ በመነሳት የተካተተ ነው።

በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 አንድ ተከሳሽ ከቀረቡበት ክሶች መካከል ከፊሉ በወታደራዊ ፍርድ ቤት ከፊሉ ደግሞ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚያስከስሰው ከሆነ በበፊቱ አዋጅ 1100/2011 ሁሉም ክሶች ከባድ ቅጣት የሚያስከትለውን ወንጀል የማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ተጠቃሎ እንደሚታይ ይደነግጋል። በዚህ የድንጋጌ አግባብ መሰረት መደበኛ ፍርድ ቤት ተጠቃሎ የሚታይ ከሆነ የሰራዊቱ የግዳጅ ባህርይና ቦታ አንፃር አመቺነት የሌለውና ለእንግልት የሚዳርግ ስለሆነ የተቀላጠፈ የፍርድ ሂደት እንዳይኖር ስለሚያደርግ በማሻሻያው ከላይ የተጠቀሰው አይነት ጉዳይ ሲኖር ሁሉም ክሶች በወታደራዊ ፍርድ ቤት ተጠቃሎ እንዲታይ በሚል ማስተካከያ ተደርጓል።

2.14. ***<u>አንቀፅ 44 ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ስለሚሰሩባቸው የሥነ-ሥርዓት ህጎች</u>፡-*** በነባሩ አዋጅ 1100/2011 በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች በወንጀል ስነ ስርዓት ህጎች መሰረት እንደሚያስችሉ ይደነግጋል። በማሻሻያው እንዳስፈላጊነቱ የፍትሀብሔር ስነ ስርዓትና የማስረጃ ህጎች ጭምር እንዲያስችሉ ተካቷል። ምክንያቱም ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ከወንጀል ጋር የተያያዙ የፍታብሄር ጉዳዮችንም አካቶ እንዲያይ ማስቻሉ ሠራዊቱ መደበኛ ፍርድ ቤት እንዳይንከራተትና በዚህ ምክንያት ሊኖር የሚችለውን የጊዜ፣ የመጉላላትና ወጪ መዳረጎችን ለመቀነስ ያስችላል ከሚል መነሻ ነው። ይህ ጉዳይም አዲስ በተዘጋጀው የወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ላይም ተካቶ ይገኛል።

2.15. ***<u>አንቀፅ 45 ስለወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት፣የሥራ ዘመንና ከዳኝነት ስለመነሣት</u> (በአዋጅ አንቀፅ 44 የነበረ)፡-*** በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ዳኞችን የመሾም ስልጣን አስመልክቶ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኛ በመከላከያ ኤታማዦር ሹም አቅራቢነት በመከላከያ አዛዦች ካውንስል እንደሚሾሙ የሚደነግገው ድንጋጌ ፍትህ አሰጣጡ ፍትሃዊነትና ገለልተኛነትን ያረጋገጠ እንዲሆን ዳኞች የመሾም ስልጣን የመከላከያ ሚኒስትሩ እንዲሆን በማሻሻያው ተስተካክሏል።

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለ ሜዳይ ሽልማት</u>

በረቂቁ አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 3 ከፊደል ሀ/ እስከ ቀ) የተዘረዘሩት የሜዳይ አይነቶች በአዋጅ 1100/2011 እና ቀጥሎ በወጣው ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1232/2013 ያልተሸፈኑ ተጨማሪ ሜዳዮች ማሻሻያው ያካተተ ሲሆን በሜዳይ ደረጃ ቅድመ ተከተል አንፃር ሲታዩም ከላቀ የስራ ውጤት ሜዳይ ቀጥሎ የሚቀመጡ ናቸው።

በረቂቁ ላይ ከላይ በተጠቀሰው አንቀፅ የተመላከቱት ተጨማሪ ሜዳዮችን ማካተት ያስፈለገው በአዋጅ የሚታወቁት ሜዳዮች እንደሚታወቀው በጦርነት ሜዳ ወይም በአውደ ውጊያ ከሚጠበቀው በላይ የተለየ ጀብዱ የሰራን ሰው መነሻ የሚያደርግ ነው። ነገር ግን በሚጠበቀው ደረጃ ግዳጅን በመፈፀም እንደአሃድ ለሚገኘው ጀብድ አስተዋፅኦ ያደረጉ አባላትን ለማበረታታትና ወደአውደ ውጊያ ሜዳይና ከዛ በላይ ላሉ ከፍተኛ ሜዳይ ለመሸለም የሚበቁ ጀግኖችን ለማፍራት ፋይዳ ይኖረዋል። በሌላ መልኩ ሲታይ የተቀመጡት ሜዳዮች አውደ ውጊያ ላይ በቀጥታ በመፋለም ጀብዱ የሠሩትን ብቻ ያማከለ ነው። የውጊያ ድጋፍና የውጊያ አገልግሎት ድጋፍ ዘርፍ ተሰማርተው ለድሉ ውጤት የጀርባ አጥንት ሆነው ያገለገሉና የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው አባላት ለመሸለምና ለማበረታታት የሚያስችል ሁኔታ የለም። የተጠቀሱት ሜዳዮች ቢያንስ በክፍሎች ደረጃ የሚሰጡ ሆነው አባላትን ለማበረታታትና የሽልማት አሰጣጡ በተቻለ መጠን አካታች (inclusive) እንዲሆን ለማድረግ የገባ ነው። እነዚህ የሜዳይ አይነቶች ከሜዳይ ሽልማት በተጨማሪ የገንዘብ ወይም የአይነት ሽልማት ከሚያስገኙ ጎራ የሚመደቡ ሲሆኑ የሽልማቱ መጠን በደንብና በመመሪያ እንደሚወሰን ታሳቢ ይሆናል።

ሌላው ማሻሻያ የተደረገው የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ሲሆን ከአንደኛ ደረጃ እስከ ሶስተኛ ደረጃ የነበረው እስከ አምስተኛ ደረጃ ከፍ እንዲል ተደርጓል። እንደሚታወቀው የሜዳይ ሽልማቱ መነሻ የሚያደርገው የውትድርና አገልግሎት ቆይታን ሆኖ የተሻለ አገልግሎት ቆይታ ያለውን በደረጃው የአገልግሎት ሜዳይ በመሸለም እውቅና ለመስጠት ነው። ሜዳይ ደረጃውን ወደ አምስት ከፍ እንዲል የተደረገበት ምክንያት በየሜዳዩ ደረጃ የተቀመጠው የአገልግሎት ጊዜ ቆይታ ተመን ሰፊ ስለነበር አባላት የውትድርና አገልግሎት ሜዳይ ለማግኘት የሚወስድባቸውን ሰፊ ጊዜ ለማጥበብ ያለመ ነው።